IBO IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

M05/1/A1AMH/SP1/AMH/TZ0/XX

22050015

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Tuesday 3 May 2005 (morning)
Mardi 3 mai 2005 (matin)
Martes 3 de mayo de 2005 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a commentary on one passage only. It is not compulsory for you to respond directly to the guiding questions provided. However, you may use them if you wish.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire sur un seul des passages. Le commentaire ne doit pas nécessairement répondre aux questions d'orientation fournies. Vous pouvez toutefois les utiliser si vous le désirez.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario sobre un solo fragmento. No es obligatorio responder directamente a las preguntas que se ofrecen a modo de guía. Sin embargo, puede usarlas si lo desea.

## ከሚከተሉት ምንባቦች አንዱን መርጠህ አስተያየትህን ስጥ(ስጭ)::

**1. (ሀ)**

ከዚያ በፊት በስብሰባችን የግጥም ንባብ ተሰምቶ ስለማያውቅ በዛሬው ስብሰባ ግጥም ይኖራል ብሎ ያሰበ ተማሪ አልነበረም።

ለአምባሳደሩ ዲስኩር የተሰጠው ጭብጨባ ሲያከትም አምባሳደሩ ተመልሰው ከተቀመጡ በኋላ፣ የሚቀጥለው ፕሮግራም የግጥም ንባብ መሆኑንና አንባቢውም የታወቀው ደብተራችን መንግስቱ ለማ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ አስታወቀ። ቀጥሎም በሁለት እጆቹ በፈረንጅ ደንብ ወደኔ አመልክቶ እንድነሳና እንድናገር ጋበዘኝ። ስነሳ ምድረ ተማሪ ጭብጨባውን አቀለጠው። እኔም በኮቴቤ የሃይማኖት ሰባኪ በነበርኩበት ጊዜ የሠለጠንኩበትን አነጋገርና የግጥም አነባብ ዘዬ ብቅ አደረግሁትና "ዛሬ በዚች በተቀደሰችዋ ቀን" በማለት ጀምሬ በዚያ የምግብ አዳራሽ ለተሰበሰቡት ክቡራንና ክቡራት የማነበው የፍቅር ግጥም መሆኑን በቁም ነገር አስታወቅሁ። ተሜ ሆዬ በፍቅር ምክንያት "እቴ ባንቺ ሰበብ ባንቺ የተነሳ፣ ዲቁናውም ቀረ ዳዊቱም ተረሳ" የሚለው የጥንቱ ባህላዊ ግጥም ትንቢት በመንግስቱ ለማ ተፈፀመ ብሎ የሚያምን ስለነበረ፣ በሳቅ ይንከተከትና አንዳንዱም ይንፈራፈር ጀመር። ሳቁም ጭብጨባውም ብዙ ጊዜ ቆየ። ወዲያው ግን ክቡር አምባሳደሩ ባሉበት እንዲህ መዝናናት የክቡርነታቸውን ክብር ከመድፈር ሊቆጠር እንደሚችል፣ የክቡርነታቸውን አለመሳቅና አለማጨብጨብ፣ እንዲያውም የግምባራቸውን መቋጠር በማየታቸው ባለፈንጠዝያዎቹ ደነገጡና ጫጫታቸውን አቋረጡ። በዚያ ፈንታ ዝምታና ፀጥታ ተተካ። ይህን ጊዜ እኔ "ዛሬ በዚች በተቀደሰችዋ ቀን የማነበው አጭር የፍቅር ግጥም ነው" አልኩና፣ "ግጥሟ በዚሁ ሰሞን አዲስ የተደረሰች ናት አርእስቷ 'በጠራ ጨረቃ' ነው" ስል ጭብጨባው አገረሸና በክቡር አምባሳደሩ ዝምታ ምክንያት ወዲያውኑ በረደ። "በጠራ ጨረቃ" አልኩና ጀመርኩ፣

> በጠራ ጨረቃ በእኩለ ሌሊት፣
> ዓይኖቿ እያበሩ እንደ ከዋክብት፣
> "ሳማት! ሳማት!" አሉት፣
> "እቀፍ! እቀፋት!። "
> እላወላወለም ወጣቱ ታዘዘ፣
> ወገቧን አንገቷን፣ እጇን በእጁ ያዘ።
> ምንም እንኳ ጡቷ እንደሾህ ቢዋጋ፣
> ጣቷ በመሆኑ የጉማሬ አለንጋ
> ጆሮ ግንዱን ሰማው በጥፊ ሲናጋ።

እዚህ ላይ ምድረ ተሜ በሳቅ ሆዱን እስኪያመው ተንከተከተ።

> ዋ ጀማሪ መሆን ! ዋ ተማሪነት፣
> ዋ ትዕዛዝ መፈፀም ዋ ምክር መስማት!
> በጠራ ጨረቃ በኩለ ሌሊት።

ተሜ ጭብጨባውን ለቀቀው፤ "ብራቮ! ብራቮ መንግስቱ ለማ!" አለ፤ መንግስቱ ለማም እጅ ነስቶ ከተቀመጠ በኋላ ሁለት ጊዜ ያህል እየቆመ ደጋግሞ እጅ በመንሳት የጭብጨባውን በረከት ተቀበለ። ክቡርነታቸው ሳይቀሩ አጨብጭበዋል። ግን የሳቸው ዝግ ያለ ከመሆኑ በላይ ድምጹ የማይሰማ ጭብጨባ ነበር። ምናለ ከዚያ በኋላ የተማሪው ሁሉ ሳቅና ስላቅ ወደ ትግርምት ወደ አድናቆት፣ ባንድ አፍታ ተለወጠ። በመካያው ዓይን ያወጣ አፍቅሮትና አክብሮት ሆነ። እኔም ከልቤ "ዛሬ ነው ድሌ!" ብዬ ጨፈርኩ። መሳቂያ መሳለቂያነቱ ከኔ ተገፎ ተነስቶ በዚያች "በጥፊ ባጮለችኝ" ቆንጆ ላይ እንደማይለቅ የሙጫ ጭቃ ተለጠፈ። ቆንጂቷ በምሳው ላይ እንደኛቿ መሃከል ተቀምጣ በልብሷ ሆነ በወሬና በጨዋታ እንደ አጥቢያ ኮከብ ተንፀባርቃ ስለነበረ፤ የተማሪው ዓይን ሁሉ ሲያርፍባት ጊዜ በድንገት ከድል አድራጊነት ተራራ ወደ ዓይን አፋርነት ኮረብታና ከዚያም ወደ እፍረትና ሐፍረት ሸለቆ ስታዘቀዝቅ፣ እዚያው በዚያው ዓይን ባይን ታየችኝ። እኔም ነገሩ ሁሉ ተዘዋውሮ መሳቅያና መሳለቂያዋ እሷ በመሆኗ አንጀቴ ነበር የራሰው።

ክቡር አምባሳደሩ ግን ያ ሁሉ ሰው ሲስቅ እሳቸው ፍንክችም አላሉ፣ ሳቅ የሚሉት አልዞረባቸውም። እመኪናቸው ድረስ ልንሸኝ አጅበን ተከተልናቸው። ከግብር ቤቱ ሲወጡ ሳለ ቆም አሉና እኔን ጠሩኝ። ጠጋ ስል "አንተ መንግስቱ ለማ የምትባለው የኮተቤ ተማሪ የነበርከው አይደለህም?" አሉ። "ነኝ" አልኳቸው" አዎ፣ የሰው ፊት አልረሳም፣ አስታውሳለሁ። ያን ጊዜ ፊደል ይሻሻላል ብለን ስንከራከር ሳለ ሳይገባህ ነው ያስቸገርከው። ኤምባሲ ናና ከዚያ እንከራከርና አስረዳሃለሁ" አሉኝ። እጅ ነሳሁ። በዚያ በታላቁ ጉባኤ ላይ ክርክሩ ተጧጡፎ ሳለ ሳይታሰብ ከክርክሩ ጥልቅ ብዬ ገብቼ ሐሳባቸውን ውድቅ በማድረጌ ቂም ሳይዙብኝ ሊያስጠጉኝ፣ ሊያስተምሩኝ፣ ሊያስረዱኝ ክቡር ፈቃዳቸው መሆኑ እንድወዳቸው አደረገኝ። እሳቸው ግን "በጠራ ጨረቃ"ን አልወደዱልኝም። "ያሰማኸው ግጥም ምን ዓይነት ትምህርት እንደሚሰጥ አልገባኝም" ብለውኝ ከዞጣ መኪናቸው ገብተው ወደ ሎንደናቸው ተመለሱ። ለኔ ግን በዚህ የፍቅር ጥፊ ሳቢያ ከደረሰብኝ ሁሉ የተማርኩት አንድ ትምህርት ነበረ፣ ያም ትምህርት በሐሰት ስም ለሚያጠፉ፣ መሳቂያ መሳለቂያ ለሚያረግና ለሚያናድድ ተንኮለኛ ሁሉ መድኃኒቱ እውነቱን ይዞ ነጋ ጠባ መጋተር ሳይሆን፤ ሐሰት መሆኑን እያወቁ" አዎ እርግጥ ነው፣ እውነት ነው" ብሎ በማመንና መስማማት፣ ከሱ ጋር አብሮ በራስ መሳቅ መፍለቅለቅ ነበር። ችግሩ ሁላችንም በሌላ ሰው መሳቅን ስንወድ፣ በገዛ ራሳችን የመሳቅ ስጦታና ችሎታ ያለን ግን በጣም ጥቂቶች መሆናችን ነው።

መንግስቱ ለማ፣ መንግስቱ ለማ፣ ደማሙ ብእረኛ ፣ ሜጋ፣ 1988::

– ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ምን ይመስልሀል?

– አስቂኝ አቀራረቡ ለጽሁፉ ያለውን አስተዋጽኦ አብራራ::

– በጽሁፉ ውስጥ የዘይቤን ጥቅም አስረዳ::

– መቼቱ ገፀባህሪያቱን በማሳየት ረገድ ያለውን አስተዋፅዎ ግለፅ::

**1. (ለ)**

# ስብሰባ

ሀሳብ - ሀሳብ - ሀሳብ
አንዱ ሲናገረው
እኛም ስንሰማው
ሌላኛው ሲያመልጠን
ደግሞ ከሌላው ዘንድ
ሌላ ሀሳብ ተገኝቶ፣
ባሳብ ሲመስጠን
ሀሳብ - ሌላ ሀሳብ
ደግሞም ሌላ ሀሳብ
በቃ ይሄው ጉዳይ
ሲፈታ ሲቋጠር
አለ የኛ ነገር።
ሁሉም ሃሳብ ብቻ
ከጠዋት እስከ ማታ
የሃሳብ ጋጋት
የሃሳብ ውካታ
ሲምታታ - ሲምታታ
የፈሰሰው ሃሳብ
እኛም የሰማነው
ዞር ስንል ጠፋ
በተግባር ሳናየው።
ዛሬም - ሆነ ነገ ካልተተገበረ
ሃሳብ ያው ሃሳብ ነው፤
ደመና ላይ ያለ።

አለሚቱ ደመና፣ <u>ባትጋራኝ፣</u> ኢሜጅ ማተሚያ ቤት፣ **1994**።

- የግጥሙ ዋና ጭብጥ ምንድነው?
- ገጣሚዋ በአንባቢው አመለከከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመችባቸው ዘይቤዎች ላይ አስተያየት ስጥ።
- በግጥሙ ውስጥ ስብሰባ እንደምን ቀርብዋል?
- ስለግጥሙ ያለህ አጠቃላይ አስተያየት ምንድነው?